የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፶
አዲስ አበባ ጥር ፲፭ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

FIFTH YEAR NO.50
ADDIS ABABA 23TH JANUARY, 2013

**ማውጫ**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
የትራንስፖርት ፕሮጀክቶች ማስተባበሪያ
ደንብ……..................…………………ገፅ ፭፻፶፱

**CONTENTS**

ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT
TRANSPORT PROJECT COORDINATION
REGULATION……………………..…Page 559

## ደንብ ቁጥር ፶/፪ሺ፭
## በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራንስፖርት ፕሮጀክቶች ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤትን ለማቋቋም የወጣ ደንብ

የአዲስ አበባ ከተማ ፈጣን የህዝብ እድገትና የከተማዋን መስፋፋት ተከትሎ እየሄደ ያለው የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ የሚፈጥረውን ዝውውር መሸከም የሚችል ተደራሽ፣ ፈጣን፣ ቀልጣፋና ምቹ የሆነ የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲኖርና ስራው በቴክኖሎጂ እንዲደገፍ ማድረግ በማስፈለጉ፤

በከተማዋ ያለውን የመሬት አጠቃቀም ፕላን ከትራንስፖርት ፕላን ጋር ተጣጥሞ ተግባራዊ እንዲሆን በማድረግ አላስፈላጊ የመሬት ብክነትን ማስወገድ፣ አስተማማኝ የትራንስፖርት መረብ እንዲሁም የተሳለጠ የትራፊክ ፍሰት ወሳኝና መሰረታዊ ጉዳይ በመሆኑና ይህንን ተልዕኮ በአግባቡ ሊወጣ የሚችል ጽህፈት ቤት ማቋቋም በማስፈለጉ፤

## REGULATION No. 50/2013
## A REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF TRANSPORT PROJECT COORDINATION OFFICE OF THE ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT

**WHEREAS,** it is found necessary to extend accessible, rapid, accelerated and suitable transport service that can bear the burden of exchanges created by the social and economic movement following the fast population growth of the Addis Ababa City and expansion of the same city as well as implement reform projects, which are supported by technology;

**WHEREAS**, it is also found necessary to establish an office that can properly discharge the basic and fundamental mission of avoiding wastage of land by implementing the land use plan of the City in compatibility with the transport plan, introducing reliable transport network as well as facilitated traffic flow;

ያንዱ ዋጋ
Unit price

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፪ ሺ፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

በተለያዩ አካላት እየተመሩ ያሉ በጅምር ሂደት ላይም ሆነ በቅድመ ትግበራ ላይ ያሉትን ፕሮጀክቶች አዋጪነት፣ ችግር ፈቺነት፣ የቴክኖሎጂውን ተስማሚነትና ዘላቂነት እያረጋገጠ ሁሉንም ፕሮጀክቶች በበላይነት የሚመራና የሚያስተባብር ጽህፈት ቤት ማቋቋም በማስፈለጉ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀፅ ፳፫(፩) (ረ) መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራንስፖርት ፕሮጀክቶች ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤትን ለማቋቋም የወጣ ደንብ ቁጥር ፶/፪ሺ፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪.ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. **"አስተዳደር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፪. **"ቢሮ" እና "የቢሮ ኃላፊ"** ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ እና የቢሮው ኃላፊ ነው፤

፫. **"ጽህፈት ቤት"** ማለት በዚህ ደንብ መሰረት የተቋቋመ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራንስፖርት ፕሮጀክቶች ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ነው፤

፬. **"ቦርድ"** ማለት የጽህፈት ቤቱ የስራ አመራር ቦርድ ነው፤

፭. **"ሥራ አስኪያጅ"** ማለት ጽህፈት ቤቱን ለመምራት በቦርዱ የተሰየመ የበላይ ኃላፊ ነው፤

**WHEREAS,** it is further found necessary to establish an office that acts as a steering body to lead and coordinate all projects including the processes under progress or those which are found on the stage of pre-implementation being led by different bodies after proving whether or not such projects are feasible, problem solving, and approved technology sustainability;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 23(1) (f) of the Revised Charter Proclamation No. 361/2003 Cabinet of the Addis Ababa City Government issued this Regulation as follows.

**PART ONE**

**GENERAL**

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as "The Addis Ababa City Government Transport Projects Coordination Office Establishment Regulation No. 50/2013".

2. **Definitions**

Unless the context requires otherwise, in this Regulation:

1. **"Government"** means the Addis Ababa City Government;
2. **"Bureau"** or **"Bureau Head"** means the Addis Ababa City Government Road and Transport Bureau and the Bureau Head respectively;
3. **"Office"** means the City Government of Addis Ababa Transport Projects Coordination Office, which is established in accordance with this Regulation;
4. **"Board"** means the Management Board of the Office;
5. **"Manager"** means the superior head appointed by the Board to manage the Office;

**፫. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

ይህ ደንብ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

**፬. <u>መቋቋም</u>**

፩.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራንስፖርት ፕሮጀክቶች ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት (ከዚህ በኋላ “ጽህፈት ቤት” እየተባለ የሚጠራ) ህጋዊ ሰውነት ያለው የአስተዳደሩ መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፣

፪. የጽህፈት ቤቱ ተጠሪነት ለስራ አመራር ቦርድ ይሆናል፡፡

**፭. <u>የጽህፈት ቤቱ ዓላማ</u>**

፩. የአዲስ አበባ ከተማ ትራንስፖርት አገልግሎት ለማሻሻል የተጀመሩና ለመጀመር በሂደት ላይ ያሉ ፕሮጀክቶችን ማስተባበርና ማቀናጀት፣

፪. ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ አዳዲስ ፕሮጀክቶችን በማስጠናት እና የልማትና ምርምር ስራዎችን በመስራት በዘርፉ የተሻለ የመንገድና የትራንስፖርት አጠቃቀም ስርዓት እንዲዘረጋ ማድረግ፣

፫. በትራንስፖርት ዘርፍ ዘላቂነት ያለው ተቋማዊ የአቅም ግንባታ ስራዎችን መስራት፣ እና

፬. በከተማው ከትራንስፖርት ጋር በተያያዘ የእውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግርን ማድረግ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>
## <u>አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር</u>

**፮. <u>አደረጃጀት</u>**

ጽህፈት ቤቱ፡-

፩. የስራ አመራር ቦርድ፣

፪. ስራ አስኪያጅ፣

፫. የፕሮጀክት ተጠሪዎች፣ እና

፬. ለስራ አስፈላጊ የሆኑ የስራ ክፍሎችና ሰራተኞች ይኖሩታል፡፡

**3. <u>Scope of Application</u>**

This Regulation shall be applicable in the City Government of Addis Ababa.

**4. <u>Establishment</u>**

1. The Addis Ababa City Government Transport Projects Coordination Office, (hereafter referred to as “Office”) is hereby established as one offices of the City Government having legal personality;
2. The Office shall be accountable to the Board.

**5. <u>Objective of the Office</u>**

1. Coordinate and integrate projects which are already started and under process for commencement in order to improve the transport service of the Addis Ababa City;
2. Facilitate the study of other necessary and new projects and carry out development and research activities, promote extension of better road and transport utilization system in the sector;
3. Accomplish institutional capacity building activities in the transport sector; and
4. Promote transfer of knowledge and technology in connection with transport service of the City.

## <u>PART TWO</u>
## <u>ORGANAIZATIONAL STRUCTURE, POWER AND FUNCTION</u>

**6. <u>Organizational Structure</u>**

The Office shall have:

1. Management Board,
2. Manager,
3. Project representatives, and
4. The necessary work units and staffs.

**፯. የቢሮው ስልጣንና ተግባር**

ቢሮው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺ፬ አንቀጽ ፵፫ የተሰጠው ስልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው ለዚህ ደንብ አፈፃፀም የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. የጽህፈት ቤቱን ስራ በተመለከተ አመራርና አቅጣጫ ይሰጣል፣ የማስተባበር ስራ ይሰራል፣ የስራ አፈጻጸሙን በመገምገም ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣ አስፈላጊና ህጋዊ እርምጃዎችን ይወስዳል፤

፪. ከፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ የሚላክለትን የፋይናንስ፣የስራ እቅድና ሪፖርት በመመርመር ለከተማው ከንቲባ በማቅረብ ይሁንታ ሲያገኝ ከፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ ጋር በጋራ በመሆን ለቦርዱ እዲቀርብና እንዲፀድቅ ያደርጋል፤

፫. አዳዲስ የትራንስፖርት ፕሮጀክቶችን በመመርመር ጠቀሜታ ያለው መሆኑን በመመዘን ውሳኔ ይሰጣል፤

፬. የቢሮ ሠራተኞች ለፕሮጀክቱ መሳካት አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ ከጽህፈት ቤቱ ጋር በመመካከር ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፤

፭. ለፕሮጀክቱ የተመደበ በጀት በአግባቡ በስራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፤

፮. በውጪ አካላት ውል የሚከናወኑ ተግባራትን ከፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ ጋር በመመካከር ይወስናል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤ ችግር ሲያጋጥም መፍትሄ ያፈላልጋል፤

፯. የፕሮጀክቱን ዓላማ ሊያፋጥኑ የሚችሉ ስልቶችን ከጽህፈት ቤቱ ጋር በጋራ በመሆን ይቀይሳል፤ የሚመለከታቸውን አካላት ያስተባብራል፡፡

**፰. የቦርድ አባላት እና የስራ ዘመን**

፩.የቦርዱ ተጠሪነትና አባላት፡-

ሀ.የቦርዱ ተጠሪነት ለከተማው ከንቲባ ይሆናል፤

ለ. የቦርዱ አባላት በከተማው ከንቲባ ይሰየማሉ፤

**7. Power and Function of the Bureau**

Without prejudice to the powers and functions vested to it pursuant to Article 43 of the City Government of Addis Ababa Executive and Municipality Service Organs Re-establishment Proclamation No. 35/2012 the Bureau shall have the following powers and functions፡

1. give direction regarding the functions of the office; accomplish coordination tasks, evaluate the work performance, monitor and provide assistance; take necessary and legal measures;
2. evaluate financial, action plan and report sent to it from the project office and submit same to the Mayor of the City and present same to the Board together with the project office to seek approval;
3. assess new transport projects and make decision after weighing for its importance;
4. in consultation with the Office create conducive conditions for the staffs of the Bureau to contribute towards the achievement of the project;
5. supervise proper utilization of the budget allocated for these projects;
6. in consultation with the Office determine activities and monitor the implementation and progress of the activities that need to be outsourced and seek solution for encountered problems;
7. design, in coordination with the Office, strategies and coordinate concerned bodies that will speed up the implementation of the objective of the project.

**8. Members of the Board and Terms of Office**

1. Accountability and Members of the Board፡
   a. The Board shall be accountable to the Mayor of the City;
   b. Members of the Board shall be appointed by the Mayor of the City;

ሐ. የቦርዱ ቃለ ጉባኤ ያዥ በስራ አስኪያጁ አቅራቢነት የሚመደብ ሆኖ ቦርዱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

፩.የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ………..ሰብሳቢ፤
፪.የትራንስፖርት ሚኒስቴር ሚኒስትር ……………………….…ምክትል ሰብሳቢ፤
፫.የመንገድና ትራስፖርት ቢሮ ኃላፊ…………………….………….አባል፤
፬.የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር……………………..…..…አባል፤
፭.የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ ኃላፊ…………..….………….…..…አባል፤
፮.የከተማ ፕላንና መረጃ ኢንስቲትዩት ዳይሬክተር………………..……..አባል፤
፯.የኢትዮ ቴሌኮም ስራ አስፈፃሚ…....አባል፤
፰.የመረጃ መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ዳይሬክተር…………………….…..አባል፤
፱. የአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን ስራ አስኪያጅ……………………......አባል፤
፲.የአንበሳ የከተማ አውቶብስ አገልግሎት ድርጅት ስራ አስኪያጅ…………….አባል፤
፲፩.የጽህፈት ቤቱ ስራ አስኪያጅ (ያለድምፅ)……………..…አባልና ፀሐፊ፤
፲፪.እንዲሁም ሌሎች እንደአስፈላጊነቱ በከንቲባው የሚሰየሙ አባላት ይኖሩታል፡፡

፪. የቦርዱ የስራ ዘመን የፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ የስራ ዘመን ይሆናል፡፡

## ፱. የቦርዱ ስልጣንና ተግባር

ቦርዱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. የጽህፈት ቤቱን የአሰራር፣ ፖሊሲዎችና መመሪያዎች ያወጣል፤

፪. የጽህፈት ቤቱን ዓመታዊ የስራ ዕቅድና በጀት በመመርመር ያፀድቃል፤

c. The Secretary of the Board shall be assigned based on the proposal of the manager and the board shall have the following members:

1. Mayor of Addis Ababa City ……………………………..…Chairperson;
2. Minster of the Ministry of Transport………..…..…Vice Chairperson;
3. Head of Road and Transport Bureau……………………….………..Member;
4. Addis Ababa City Police Commission Commissioner ……………..……..Member;
5. Land Development and Management Bureau Head ……….………………Member;
6. Urban Planning and Information Institute Director…………………………..Member;
7. Ethio -Telecom Executive…….….Member;
8. Director of Network and Information Security Agency ………………….. Member;
9. Manager of Addis Ababa City Roads Authority …………..………….... Member;
10. Manager of Anbesa City Bus Service Enterprise ……………….……… Member;
11. Manager of the Office (without vote) ……….……….....Member and Secretary;
12. Other members assigned by the Mayor of the City, where necessary.

2. The term of Office of the Board shall be the term of office of the Project Office.

## 9. Power and Function of the board

The Board shall have the following power and functions:

1. issue the work procedures, policies and directives of the office;
2. examine and approve the annual action plan and budget of the Office;

፫. የትራንስፖርት ፕሮጀክቶቹን አፈፃፀም ቅልጥፍና እና ጥራት እገዛ የሚያደርጉ ባለድርሻ አካላት ተግባራቸውን በአግባቡ እየፈፀሙ መሆኑን በማረጋገጥ ተገቢውን ሁሉ እንዲያከናወኑ ድጋፍ ያደርጋል፤

፬. የትራንስፖርት ፕሮጀክቶቹን ማስፈፀሚያ በጀትና የበጀት ምንጭ ተጠንቶ ሲቀርብለት በሚመለከተው አካል እንዲመደብ ያደርጋል፤

፭. የጽህፈት ቤቱ ስራ አስኪያጅ በቢሮው ኃላፊ ተመልምሎ ሲቀርብለት ተገቢነቱን በማረጋገጥ ይሾማል፤

፮. የጽህፈት ቤቱን ስራና የበጀት አፈፃፀም ሪፖርት በየወቅቱ መርምሮ ያጸድቃል፤ ለከተማው ከንቲባም ያቀርባል፤

፯. የጽህፈት ቤቱን የስራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ደረጃና ደመወዝ እንዲሁም የሚተዳደሩበትን ስርዓት ይወስናል፡፡

## ፲. __የቦርዱ የስብሰባ ስነ-ስርዓትና ውሳኔ__

፩. ቦርዱ በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል፤ ሆኖም ሰብሳቢው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፤

፪. የቦርዱ ስብሰባ ከቦርዱ አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፤

፫. የቦርዱ ውሳኔ የሚያልፈው በስብሰባው ከተገኙ የቦርዱ አባላት ከግማሽ በላይ ሲደገፍ ይሆናል፤ ሆኖም ድምፅ እኩል በሚሆንበት ጊዜ ሰብሳቢው የደገፈው የቦርዱ ውሳኔ ይሆናል፤

፬. የቦርዱ አባላት የሚወስኑት ማንኛውም ህገ-ወጥ ውሳኔ ለሚያስከትለው ኃላፊነት በዕለቱ በውሳኔው ላይ የተገኙ አባላት በጋራም ሆነ በተናጠል ተጠያቂነት አለባቸው፤ ሆኖም በውሳኔው የልዩነት ሀሳብ ያስቀመጠ ተጠያቂነት አይኖርበትም፡፡

3. ensure and support stakeholders that are contributing to the effectiveness and quality of the transport projects;
4. cause the allocation of budget by the appropriate entity for the budget and its source studied and submitted to it for the implementation of the transport projects;
5. appoint Manager of the Office by ensuring the appropriateness upon the recommendation of Head of the Bureau;
6. timely examine and approve the work performance and budget utilization reports of the office; submit same to the Mayor of the City;
7. determine the grade and salary of officials and staffs of the office; determine operation procedure manual.

## 10. __Meeting Procedure and Decision of the Board__

1. The Board shall hold regular meeting once in a month; however, the Chairperson may call an extraordinary meeting at any time, if necessary;
2. The presence of more than half of the members of the Board shall constitutes a quorum;
3. Decisions of the Board require the approval of the majority members present and voting; in case of a tie the Chairperson shall have a casting vote;
4. Each member who has voted for the decision shall be jointly and severally liable where the decision of the Board violates the law; however, a member who sets his points of difference on the same decision shall have no liability.

**፲፩. <u>የፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ ስልጣንና ተግባር እና የስራ ዘመን</u>**

ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. በአዲስ አበባ ከተማ ያለውን የትራንስፖርት እና ትራፊክ ማኔጅመንት ለማሻሻል የሚቀርቡለትን ጥናቶች በመመርመር ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤ ሲፈቀድለትም ይፈፅማል፣ ያስፈፅማል፤

፪. በከተማው ውስጥ ከተለያዩ የልማት አጋሮች ጋር በመሆን የተጀመሩ የትራንስፖርት አገልግሎትና የትራፊክ ማኔጅመንት ማሻሻያ ፕሮጀክት በተቀመጠላቸው አቅጣጫ፣ በተገባው ውልና ስምምነት እንዲሁም የስራ ዝርዝር መሰረት እየተፈፀሙ መሆኑን ይከታተላል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፫.በከተማ ውስጥ የሚካሄዱ የትንስፖርት ፕሮጀክቶች ሲጠናቀቁ የአገልግሎት ስራን የሚመራ ተቋም በመለየት ወይም እንዲደራጅ በማድረግ የአገልግሎት ስራው እንዲጀመር ያደርጋል፤

፬. የከተማውን ትራንስፖርት ለማሻሻል የተመረጡ ፕሮጀክቶች ትግበራ ላይ የአማካሪዎች፣ የአቅራቢዎች እና የኮንትራክተሮች ማወዳደሪያና መምረጫ መስፈርቶች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤ እንደአስፈላጊነቱም በሌሎች ተቋማት እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤

፭. አጠቃላይ የከተማ ትራንስፖርትና ትራፊክ አመራር የማሻሻል ስራዎችን በሚመለከት ቢሮውን የማማከር ስራ ያከናውናል፤

፮. እንደአስፈላጊነቱ በቦርዱ እና በቢሮው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

**፲፪. <u>የጽህፈት ቤቱ የሚቆይበት ጊዜ</u>**

የፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ የቆይታ ጊዜ ላልተወሰነ ጊዜ ሆኖ በየሁለት ዓመቱ እየተገመገመ የከተማው ካቢኔ በሚሰጠው ውክልና መሰረት በቦርዱ የቆይታ ጊዜውን ይወሰናል፡፡

**11. <u>Power and Function of the Project Office</u>**

The Office shall have the following powers and functions:

1. examine and submit studies to improve transport and traffic management existing in Addis Ababa City to the concerned body; implement, enforce the implementation of the same up on approval;
2. monitor the performance of the transport service and traffic management reform projects that are being undertaken in accordance with the set targets, contracts and agreements as well as work specifications in collaboration with different development partners; put the same in to practice;
3. identify institutions that will be in charge to lead service activities or facilitate the organization of such institution to commence the service up on completion of transport projects, which are being carried out in the City;
4. facilitate the preparation of requirements to be met for selection and identification of consultants, suppliers and contractors for the implementation of selected projects to improve the transport service of the City; refer same to be prepared by other institutions as the need arises;
5. consult the Bureau on activities concerning transport and traffic order improvement in the City;
6. Perform such other tasks assigned to it by the Board and the Bureau, if necessary.

**12. <u>Duration of the Office</u>**

The duration of the Office shall be for unlimited period of time and the performance of the Office shall be subjected to evaluation every two years and determined by the Board based on the delegation provided by the Cabinet of the City.

፲፫. **<u>የጽህፈት ቤቱ ስራ አስኪያጅ ስልጣንና ተግባር</u>**

፩. የጽህፈት ቤቱ ዋና ስራ አስፈፃሚ ሆኖ ያገለግላል፣ ጽህፈት ቤቱን በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ያስተዳድራል፤

፪. የጽህፈት ቤቱን ስልጣንና ተግባር በስራ ላይ ያውላል፤

፫. በትራንስፖርት ማሻሻያ ላይ ወደ ተግባር ለገቡ ፕሮጀክቶች ለእያንዳንዳቸው የፕሮጀክት ተጠሪ እንዲመደብ ያደርጋል፤

፬. የጽህፈት ቤቱን ዓመታዊ የስራ ዕቅድና በጀት በማዘጋጀት ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፭. ለጽህፈት ቤቱ በተመደበ በጀትና የስራ ዕቅድ መሰረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤ በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፤

፮. የትራንስፖርት ፕሮጀክቶችን መሰረት በማድረግ ከሶስተኛ ወገን ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ጽህፈት ቤቱን ይወክላል፤

፯. የጽህፈት ቤቱን የስራ እንቅስቃሴና የሂሳብ ሪፖርት በወቅቱ አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፤ በተጨማሪም በቦርዱ የጸደቀውን የሂሳብ ሪፖርት ለከተማው አስተዳደር ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ይልካል፣

፰. የፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱን ሰራተኞች በቦርድ በሚወስነውና አግባብ ባለው ህግ መሰረት ይቀጥራል፣ ያሰናብታል፣

፱. ስራ አስኪያጁ በከተማው የሚካሄዱ ትራንስፖርት ነክ ፕሮጀክቶችን ያማክራል፤ ያስተባብራል፤ ይመራል፣

፲. የትራንስፖርት ማሻሻያ ጥናቶችና ሃሳቦች መሰረት በማድረግ በቢሮ ኃላፊው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፣

፲፩. በቢሮው ስር ያለውን የሰው ኃይል ከትራንስፖርት ፕሮጀክቶች አንጻር አቅም ግንባታ ተግባራት እቅዶ እንዲከናወኑ ያደርጋል፣

፲፪. በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

**13. <u>Power and Function of the Manager of the Office</u>**

1. Serve as chief executive of the Office, Coordinate and superiorly administer the Office;
2. Implement powers and functions of the Office;
3. Cause the assignment of project representative for each of the projects that are in action to implement transport reforms;
4. Prepare the annual action plan and budget of the office and submit same to the board; and implement it up on approval;
5. Dispense money based on the allocated budget and action plan of the Office; and supervise the appropriate implementation of same;
6. Represent the Office in all work relationships made with third party;
7. Timely prepare and submit the performance and financial report of the Office to the board; in addition, send the financial report approved by the board to Finance and Economic Development Bureau of the City Government;
8. Hire and dismiss staffs of the project office in accordance with the decision of the Board and the relevant law;
9. Consult, coordinate and lead transport related projects which are being carried out in the City;
10. Accomplish tasks entrusted by the Bureau Head based on transport reform studies and proposals;
11. Plan and cause the implementation of human resource capacity building scheme of the Bureau;
12. Perform other activities assigned to him by the Board and the head of the Bureau.

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፲፬. የበጀት ምንጭ**

የጽህፈት ቤቱ የበጀት ምንጮች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

፩. ከአስተዳደሩ ከሚመደብ በጀት፣

፪. ከልማት ትብብርና አጋር ተቋማት ከሚገኝ ህጋዊ እርዳታና ብድር፣ እና

፫. ከሌሎች ህጋዊ ምንጮች ከሚገኝ ገቢ ይሆናል፡፡

**፲፭. የሒሳብ መዝገብ ስለመያዝ**

፩. ጽህፈት ቤቱ የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብትን ይይዛል፤

፪. የጽህፈት ቤቱን የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች የአስተዳደሩ ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት በሚሰይማቸው ኦዲተሮች ሂሳቡ እንዲመረመር ሊያደርግ ይችላል፣

**፲፮. መመሪያ የማውጣት ስልጣን**

ቦርዱ ይህንን ደንብ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፲፯. የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰዉ ይህንን ደንብ ለማስፈፀም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**፲፰. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች**

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በተመለከተ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**፲፱. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከጥር ፲፯ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ**

**ጥር ፲፭ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም.**

**ኩማ ደመቅሳ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

## PART THREE

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

**14. Sources of Budget**

The source of budget for the Office shall be from:

1. budget allocated to it by the City Government,
2. donation acquired from development cooperation and partner institutions, and
3. revenue acquired from other legal sources.

**15. Keeping of Books of Account**

1. The Office shall keep complete and accurate books of account;
2. Books of account of the Office shall be inspected by auditors to be assigned by Office of the Auditor General of the City Government.

**16. Power to Issue Directive**

The Board may issue directive for the implementation of this Regulation.

**17. Obligation to Cooperate**

Any person shall have the duty to cooperate for the implementation of this Regulation.

**18. Inapplicable Laws**

Any Regulation, directive or customary practice which is inconsistence to matters covered for in this Regulation shall have no effect.

**19. Effective Date**

This Regulation shall enter in to force as of 25th day of January, 2013.

**Done at Addis Ababa**

**23rd Day of January, 2013**

**Kuma Demeksa**

**Mayor of Addis Ababa City**